አዘጋጆች፡- ሃይሉ አርአያ (ዶ/ር)፣ ነፃነት ገነነ፣ ብርሃኑ ሃጎስ እና አስቴር በ/ፅዮን

አዘጋጆች፡- ሃይሉ አርአያ (ዶ/ር)፣ ነፃነት ገነነ፣ ብርሃኑ ሃጎስ እና አስቴር በ/ፅዮን

---

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሶርትየም

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

2013 ዓ.ም.

<u>ቢጋር/ ማውጫ</u>

1. የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምን ይመስላል ....................................................2
1.1 የአለማችን ወቅታዊ ሁኔታ ........................................................2
1.2 የአፍሪካ ወቅታዊ ሁኔታ ..........................................................2
1.3 የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ ........................................................2

2. ወረርሽኙ በኢትዮጵያ ያስከተላቸው ተግዳሮቶች ........................................3
2.1ፖለቲካዊ ቀውስ ......................................................................3
2.2የትምህርት ቤቶች መዘጋት ............................................................3
2.3ኢኮኖሚያዊ ችግር ....................................................................4
2.4ማሕበራዊና የስነልቦና ችግሮች .......................................................4
2.5ሰብአዊ ቀውስ ........................................................................5
2.6በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ያደረሰው ጉዳት ............................................5
2.7ስልጠና እና ክትትል መስተጓጎል ....................................................6

3 የአግሮኢኮሎጂ ግብርና በኮቪድ-19 ላይ ያለው ተፅእኖ ..............................7
3.1የድህረ ምርት አያያዝ እና ፈጠራዎች ...............................................7
3.2የተፈጥሮ ማዳበርያና የተባይ መከላከያ ውሁዶችን ማዘጋጀት እና መጠቀም ........7
3.3የጓሮ አትክልት ማምረት ..............................................................8
3.4 የጥምር እርሻ (አግሮፎረስትሪ) ማስፋፋት ..........................................8
3.5ማህበረሰብ-አቀፍ ንቅናቄዎችን ማከናወን ............................................8
3.6አሳታፊነትን ማበረታታት ............................................................9
3.7በኮቪድ-19 ምክንያት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች ..........................................9
3.8ለኮቪድ-19 የተደረገ ፈጣን ግብረ-መልስ ...........................................9

4 ማጠቃለያና አስተያየት ..................................................................11

# 1. የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምን ይመስላል

## 1.1 የአለማችን ወቅታዊ ሁኔታ

የኮቪድ-19 ከታህሳስ 2019 በሁዋን ከተማ በሃገረ ቻይና መታየት ከጀመረበት ግዜ አንስቶ አለም አቀፍ ስጋት በመፍጠሩ ምክንያት በጥር 30, 2020 ላይ የአለም ጤና ድርጅት ኮቪድ-19 በሽታ የአለም ማህበረሰብ የጤና ጠንቅ ነው በማለት አውጇል፡፡ እስከአሁን ድረስም ወረርሽኙ በሁሉም የአለም አገራት ላይ የተስፋፋ ሲሆን እስከ ህዳር 14, 2020 ባለው ግዜ ከየአገራቱ በተሰበሰበው መረጃ መሰረት በአለም በአጠቃላይ 53,749,202 በበሽታው የተያዙ፣ 1,309,432 ሕወታቸው ያለፈ፣ እንዲሁም 37,525,177 ከበሽታው ያገገሙ መሆናቸውን ያመለክታል፡፡ ሁኔታዎች በዚህ መልኩ ከቀጠሉ በሚቀጥሉት ወራት ወረርሽኙ በአለም ላይ ተጨማሪ ከፍተኛ የሰው ሕይወት ሊቀጥፍ እንደሚችል፤ በአለምአቀፍ የሸቀጦች አቅርቦት ሰንሰለት ላይ ትልቅ መስተጓጎል እንደሚፈጥር፤ ለግብይት የተዘጋጁ እቃዎች ዋጋ ላይ መውረድ እንደሚያሳይ እንዲሁም ባደጉም ይሁን በአዳጊ ሃገራት ላይ መጠነ ሰፊ የሆነ ኢኮኖሚያዊ ውድቀት ሊያስከትልባቸው እንደሚችል ነው በሰፊው እታየ ያለው፡፡

## 1.2 የአፍሪካ ወቅታዊ ሁኔታ

የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በአፍሪካ አህጉር ለመጀመርያ ግዜ በምርመራ አማካኝነት መገኘቱን የተረጋገጠው የካቲት 14, 2020 ላይ ሲሆን በበሽታው የተያዘ ሰው የተመዘገበባት የመጀመርያዋ አገርም ግብፅ ነበረች፡፡ በአፍሪካ ወረርሽኙ መታየት የጀመረው ከሌሎች አህጉሮች ማለትም ኤስያ፣ አውሮፓ፣ አሜሪካ ዘግይቶ ቢሆንም አህጉሪቱ ካለችበት ነባራዊ ሁኔታ አኳያ ሲታይ በሽታው በአሁኑ ወቅት የአገራቱን ደካማ የጤና መሰረተ ልማት ይበልጥ በሚያዳክም እና በሚያስፈራ መልኩ በብዙ አገራት ተስፋፍቶ ይገኛል፡፡ እስከ ህዳር 14, 2020 የተሰበሰበ መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ እስከ አሁን ድረስ በበሽታው የተያዙ 1,961,096፣ ሕይወታቸው ያለፈ 46,906፣ በአጠቃላይ ያገገሙ 1,650,731 ናቸው፡፡

## 1.3 የኢትዮጵያ ወቅታዊ ሁኔታ

በአገራችን ኢትዮጵያም የኮረና ቫይረስ በሽታ ለመጀመርያ ግዜ መገኘቱን ከተነገረበት ከመጋቢት 13, 2020 ጀምሮ ይህ መረጃ እስከተጠናቀረበት ግዜ ማለትም ህዳር 14, 2020 ድረስ ያለውን ሁኔታ ስንመለከት በአጠቃላይ 101,757 በበሽታው የተያዙ፣ 1,558 የሞቱ፣ 63,571 በበሽታው ተይዘው ያገገሙ መሆናቸውን ጤና ሚኒስተር በየቀኑ ወረርሽኙ በተመለከተ በሚሰጡት የሚድያ ማብራሪያ ላይ ገልፀዋል፡፡ ሚኒስተሩ በተጨማሪ እንደገለፁት ከሆነ እስከአሁን ድረስ የተገኘባቸው ታማሚዎች ብዛት ሲታይ አነስተኛ ይመስላል ይሁን እንጂ የተደረገው የምርመራ ብዛት (1,550,663) ሲታይ በተደራሽነት ስፋት በጣም አነስተኛ በመሆኑና በማህበረሰቡ ላይ በከፍተኛ መጠን ምርመራ ባለመደረጉ ምክንያት እንደሆነና ይህም ሊያዘናጋን እንደማይገባ ያብራራሉ፡፡ በመሆኑም ህብረተሰቡ ጥንቃቄዎችን አዘውትሮ ከመተግበር መዘናጋት እንደሌለበት ሚኒስተርዋ አሳስበዋል፡፡

## 2. ወረርሽኙ በኢትዮጵያ ያስከተላቸው ተግዳሮቶች

እንደ የአለም ባንክ ትንበያ ከሆነ ወቅታዊው የኮረና ቫይረስ (ኮቪድ-19) ወረርሽኝ በአፍሪካ ሃገራት ላይ ሊያደርስ ይችላል ብሎ ካስቀመጣቸው ተግዳረቶች መካከል፡- ከሰሃራ በታች ያሉት ሃገራት ባለፉት 25 አመታት ውስጥ ታይቶ የማይታወቅ ኢኮኖሚያዊ ውድቀት እንደሚያጋጥም፤ የ7% የእርሻ ምርቶች መቀነስ፤ እንዲሁም 25% የምግብ አቅርቦት ቅናሽ እንደሚያስከትል የሚሉት ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በኮቪድ-19 ምክንያት በኢትዮጵያ የተፈጠሩ ተግዳረቶች ምን ይመስላሉ የሚለውን በመጠኑ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

### 2.1 ፖለቲካዊ ቀውስ

ኢትዮጵያ ህገመንግስቱ ላይ በሰፈረው መሰረት በየ5 ዓመት አንዴ የምታካሂደው ምርጫ ባለፈው አመት ግንቦት ወር ላይ ይካሄድ የነበረ ቢሆንም ባለፉት ሦስት አመታት በአገሪቱ በተከሰቱ ፖለቲካዊ ችግሮች ምክንያት ምርጫው በሦስት ወር ተራዝሞ በነሐሴ 29, 2020 እንዲካሄድ ግዜ ተቆርጦለት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በመላው አለም የተከሰተውን የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በአገራችንም በመታየቱ ምክንያት በሽታው እንዳይስፋፋና ከፍተኛ ጉዳት እንዳያደርስ ለመከላከልና ለመቆጣጠር እንዲያስችል የአገሪቱ የሚኒስትሮች ምክርቤት በ8 ሚያዝያ 2020 ተሰብስቦ ለአምስት (5) ወር የሚዘልቅ የአስቸኳይ ግዜ አዋጅ እንደታወጀ እንዲሁም አዋጁ ከሁለት ቀን በኋላ በህዝብ ተወካዮች ምክርቤት እንዲፀድቅ ተደርጓል፡፡ አገርአቀፍ አዋጅ ከመታወጁ በፊትም ቢሆን የተለያዩ ክልሎች በግዛታቸው ውስጥ በተናጠል አስገዳጅ አዋጆች በስራ ላይ ያዋሉ ሲሆን በፌደራል ደረጃም መንግስት እንቅስቃሴና መሰብሰብን የሚከለክል አሰራር እንዲተገበር ማድረጉ ይታወቃል፡፡ የወረርሽኙ መስፋፋት ምርጫ በወቅቱ እንዳይደረግና ከፍተኛ ፖለቲካዊ ቀውስ እንዲፈጠር መንገድ ጠርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት በወረርሽኙ ምክንያት ከተጋረጡብን የማህበረሰብ አቀፍ የጤና እና ተያያዥ እክሎች ባልተናነሰ መልኩ በሽታው በመከሰቱ ምክንያት ምርጫ በወቅቱ ለማካሄድ አለመቻሉ አደገኛ ፖለቲካዊ ውጥረት እንዲፈጠር ምክንያት ሆነዋል፡፡ እንዲሁም የህዝቦች ህልውና እና ቀጣይነት በማስጠበቅ በኩል አገሪቱ መስቀለኛ መንገድ ላይ እንድትገኝ አድርጓታል፡፡

### 2.2 የትምህርት ቤቶች መዘጋት

የኢትዮጵያ መንግስት የኮቪድ-19 በሽታ በታየ በሦስተኛው ቀን ማለትም መጋቢት16, 2020 ላይ ባሳለፈው ውሳኔ መሰረት ሁሉም ትምህርት ቤቶች እንዲዘጉ ተደርገዋል፡፡ ከ26 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ከመዋእለ ህፃናት ጀምሮ እስከ ከፍተኛ የትምርት ተቋማት የሚማሩ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታቸው ተስተጓጉለዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ከአንድ ሚልዮን በላይ ተማሪዎችን ተጠቃሚ የሚያደርገው የትምህርት ምገባ ስርአት በወረርሽኙ ምክንያት ተቋርጠዋል፡፡ በሃገሪቱ የሚገኙ ከ50 በላይ ዩኒቨርሲቲዎች ተዘግተው ተማሪዎች በዚህ አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ወደ የመጡበት ተመልሷል፡፡ በአንዳንድ ክልሎችና የትምርት ተቋማት አማካኝነት ኢ-መደበኛ በሆነ መንገድ ማለትም በሬድዮ፣ ቴሌቪዥን፣

ማሕበራዊ ሚድያ ወዘተ አማካንነት ትምህርት ለማስቀጠል ሙከራዎች ቢኖሩም መብራት በመቆራረጥ፣ ደካማ የኢንተርኔት አገልግሎት በመኖሩ ምክንያት ሁሉም ተማሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ ኣላስቻለም። ይባስ ብሎ ደግሞ የማህበራዊ ሚድያ ተጠቃሚነት የሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እና አካባቢዎች ምንም እድል እንዳይኖራቸው ሆነዋል። ከዚያም አልፎ ልጆች እቤት መዋሉ ወደ መሰላቸት እየገቡ ስለሆነ ውጭ ለመውጣት በሚያደርጉት ሙከራዎች ከቤተሰብ እየተጋጩ ነው።

## 2.3. ኢኮኖሚያዊ ችግር

እንደ በአፍሪካ የሚገኘው የተባበሩት መንግስታት የኢኮኖሚክ ኮሚሽን ግምት ከሆነ ኢትዮጵያ በኮረና ወረርሽኝ ምክንያት በዚህ አመት የ2.7 በመቶ ብቻ እድገት እንደምታስመዘግብ ተንብዮዋል። እንዲሁም አውሮፓውያን በወረርሽኑ ስለተጠቁ በኢትዮጵያ የአበባ ምርት ሰደድ ላይ ከፍተኛ ጉዳት እንዲደርስ ያደረገ ሲሆን በዚህ ምክንያት የ80 በመቶ ዋጋ ቅናሽ አሳይተዋል፤ ከዛ አልፎ 150,000 የሚሆኑ ሰራተኞችም ስራቸው የማጣት አደጋ ላይ ናቸው። በተጨማሪም የኢትዮጵያ አየር መንገድ እንደገለፀው ከሆነ በወርሀ ጥር 2020 ብቻ የ550 ሚልዮን ዶላር ትርፍ አጥተዋል። የሆቴል ቱሪዝሙም በጣም ከተጎዱት የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ ሁነዋል። አገሪቱ በሞላ ባለው የእንቅስቃሴ እግድ ምክንያት የእርሻ ምርት አቅርቦት እጥረት በመኖሩ ህብረተሰቡ በጣም ተቸግሯል። ከዚሁም በማያያዝ ዋናው የገቢ ንግድ እቃ መስመር የሆነችው ጅቡቲ የቫይረሱ መነሻም እየሆነች ስለሄደች ሾፌሮች ሲወጡም ሲገቡም ችግር እየደረሰባቸው ስለሆነ ከጊዜ በኋላ ስራቸው ሊያቆሙ ስለሚችሉ ችግሩ ያባባሳል የሚል ግምት አለ።

## 2.4. ማሕበራዊና የስነልቦና ችግሮች

በየቦታው የሚታየው የስራ አጥ ቁጥር መብዛት ዋናው የማህበራዊ ችግር እንደሆነ ማስተዋል ይቻላል። ከዚያ ባሻገር አብዛኛው ኢትዮጵያዊ እርስ በርሱ የተቀራረበ ማሕበራዊ ትስስር ያለው ሲሆን በተለይ በለቅሶ፣ ክርስትና፣ ሰርግ፣ ድግሶች፣ ወዘተ ሰላምታው እንዲሁም በተለያዩ ማሕበራዊ ሁነቶች ላይ ተደጋግፎ የሚሰራ መሆኑ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በአሁኑ ወቅት በወረርሽኙ ምክንያት እንዲራራቅ ተገዷል። ይህም ያልተለመደ በመሆኑ በሽታውን ለመከላከል የሚደረገው ግብረ-መልስ ይህ ያዳበረው ማህበራዊ ልምድ ትልቅ እንቅፋት ሲሆንበት ይታያል። ይህ ብቻ አይደለም እንቅስቃሴው በመገደቡ ችግሩን ለመሻገር የሚያስችል በቂ አቅም ስለሌለው እና በመራራቁ ምክንያት ለከፍተኛ የስነልቦና ችግር ተዳርገዋል። ከዚህ በተጓዳኝም ሴቶች በመላው ኢትዮጵያ ውስጥ የየቤተሰቦቻቸው ትላልቅ ሃላፊነቶች የተሸከሙ በመሆናቸው ወረርሽኙ በነሱ ላይም ቀላል የማይባል ጫና ሊፈጥር እንደሚችል ይታመናል።

አንዱ እና ዋነኛው ችግር ደግሞ የሚሆነው መንግስት እና ባለሙያዎች የየአካባቢ ማህበረሰብ የቆየ ወረርሽኝ የመከላከል መልካም ልማዶች ወስዶ መጠቀም ላይ እንዲሁም ለማህበረሰቡ በሃላፊነት ማካፈል አለመቻሉ ሌላው ችግር ነው።

## 2.5 ሰብአዊ ቀውስ

እንደሚታወቀው አገራችን ኢትዮጵያ ከኮቪድ-19 ወረርሽኝ በፊትም ቢሆን በተለያዩ ገዢ ምክንያቶች ማለትም ፖለቲካዊ ችግር፣ የተፈጥሮ አደጋ፣ የአየር ንብረት ለውጥ እና በሌሎችም ምክንያቶች በተለያዩ ወቅቶች ለሰብአዊ ቀውስ ተጋላጭ ነበረች፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ የኮቪድ-19 በሽታ ወረርሽኝ ሲጨመርበት በአገሪቱ ከፍተኛ የሆነ ሰብዓዊ ቀውስ እየተፈጠረ እንደሆነ ብዙ አመላካች ማሳያዎች እየታዩ ነው፡፡ በተለይ በረሃብ የሚሞቱ ሰዎች ቁጥር እንደሚጨምር መገመት ይቻላል፡፡ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ከተለያዩ አገሮች በተለይ ከሳውዲ፣ የመን፣ ጂቡቲ፣ ሶማሊላንድ፣ ሱዳን ወዘተ በመመለስ ላይ ሲሆኑ የኮቪድ-19 በሽታ ማስተላለፍ አኳያ ብቻም ሳይሆን ወጣቶች ስለሆኑ ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች የማስተላለፍ እድላቸው ከፍ ስለሚያደርገው ፈታኝ ያደርገዋል፡፡

በኢትዮጵያ የለይቶ ማቆያ ወጪ በመንግስት የሚሸፈን ባለመሆኑ ለውሸባ የተዳረጉ ዜጎች ወጪውን በመፍራት በድብቅ እያመለጡ ከህብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀሉ ምክንያት እየሆነ ይገኛል፤ አንዳንድ ሃላፊነት የማይሰማቸው ተመላሾችም የቁጥጥር ኬላዎችን በመተው በሌሎች መንገዶች በመግባት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ባሻገር በህብረተሰቡ የግንዛቤ ብዥታ ስላለ የመከላከል እና የጥንቃቄ ግንዛቤ ችግር በሰፊው ይታያል፡፡

## 2.6 በግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ያደረሰው ጉዳት

### 2.6.1 የግብርና ግብአቶች እጥረትና ዋጋ መናር

አገራችን ኢትዮጵያ በገቢ የግብርና ግብአቶች (ኬሚካሎች እና ማዳበርያዎች) ላይ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከውጭ መግዛት ላይ ጥገኛ ስትሆን የአለም መንግስታት ዋናው ትኩረታቸው በሆነው ወቅታዊው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ ለመከላከልን ለመቆጣጠር ሲባል ድንበሮቻቸውን መዝጋታቸውና የሰዎች እንቅስቃሴ እንዲገደብ ባደረጉበት ወቅት ግብአቶች በግዢ መልክ ወደ ሃገር ውስጥ ለማስገባት አዳጋች ሆኗል፡፡ በተጨማሪ የመንግስት የፋይናንስ አቅም በወረርሽኙ ምክንያት በእጅጉ ስለሚፈታተነው ካለው ውስን ሃብት ቀንሶ ግብአቶችን ለመግዛት የሚውል ገንዘብ ለማግኘት ያዳግታል፡፡ በዚህም ምክንያት የተለያዩ ትላልቅ አለምአቀፍ አምራቾች የግብርና ግብአቶችን አምርተው ለመላክ በጣም ከባድ ያደርግባቸዋል፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያ በወረርሽኙና በሌሎች ተጓዳኝ ምክንያቶች የተለያዩ ግብአቶችን በወቅቱ ለአርሶአደሩ ለማቅረብ ፈታኝ ሆኗል፡፡

### 2.6.2 የአትክልቶች አቅርቦትና ፍላጎት መቀዛቀዝና የዋጋ አለመረጋጋት

በኮቪድ-19 ምክንያት የሃገር ውስጥ እንቅስቃሴ መገደብ የገበሬው የእርሻ ምርት ከቦታ ወደ ቦታ እንዳይንቀሳቀስ ስለተደረገና ኢ-መደበኛ የሆኑ ብዛት ያላቸው የግብይት ቦታዎች በተገቢው መንገድ አገልግሎት እንዳይሰጡ በመደረጉ በአንድ በኩል ገበሬው ገበያ አግኝቶ መሸጥ አልቻለም፤ በሌላ በኩል የደረሱ ምርቶች በተለይ አትክልት እና ፍራፍሬዎች ከማሳ ሳይነሱ ለብልሽት የመዳረግ እጣ አጋጥሟቸዋል፡፡ ስለሆነም የምርት አቅርቦት ሰንሰለቱ ስለተስተጓጉለ

የእርሻው ምርት በወቅቱ ተጓጉዞ በከተማ አካባቢ ያለ የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ እንዳይሆን ትልቅ እንቅፋት ሁነዋል፡፡ ይህም ሆኖ እያቆራረጡ ወደ ከተማ የደረሱ ምርቶች ዋጋ እንኳን ብንመለከት አንድም የሸማቹ ማህበረሰብ የማይቀመሱ ሆነዋል በሌላም ገበሬው የተሸለ ዋጋ ማግኘት አልቻለም፡፡ ችግሩ ከዚህም በላይ ወደ ውጭ የሚላኩ የግብርና ውጤቶች (ቡና፣ አበባ፣ ሰሊጥ፣ ፍርፍሬዎች፣ አትክልቶች) ላይ ከፍተኛ መስተጓጉል በመፈጠሩ አገሪቱ ማግኘት የነበረባት የውጭ ምንዛሬ እንድታጣ ምክንያት ሆነዋል፡፡

### 2.6.3 በእንስሳ ምርት ያለው ችግር

የወረርሽኙ መስፋፋት አርሶ አደሮችም ሆነ አርብቶአደሮች ለእንስሳዎቻቸው ከቦታ ወደ ቦታ ተንቀሳቅሶ ውሃና የግጦሽ መሬት ለማግኘት ትልቅ እንቅፋት ይሆንባቸዋል፡፡ ወተትና የወተት ተዋፅኦ (የመበላሸት ባሕርይ ስላላቸው) ቶሎ ለገበያ ለማቅረብ አዳጋች ያደርገዋል፡፡ የቁም እንስሳ ለመሸጥም የተመቻቸ የገበያ ስርአት አይኖርም፡፡ ባለፈው የፋሲካ በዓል (2020) ላይ ወደ ገበያ የቀረቡት የእንስሳት ቁጥር ከፈላጊው ማህበረሰብ ጋር በቁጥር ስላልተመጣጠኑ ዋጋቸው እስከ ሶስት እና አራት እጥፍ ስለነበረ ህብረተሰቡ በተገቢው መንገድ ገዝቶ መጠቀም አልቻለም፡፡

### 2.6.4 የምግብ ዋስትናና የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት ችግር

የአለም ባንክ ያወጣው ሪፖርት እንደሚያመለክተው ከሆነ ከሁሉም የንግድ ልውውጦች መካከል በከፍተኛ ሁኔታ ተጎጂ የሚሆነው ዘርፍ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ሲሆን ትልቅ ጉዳት የሚያደርሰውም በምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ስራ ላይ ይሆናል፡፡ ይህ የሚሆነውም አገሪቱ በሚኖራት ውስን የምግብ አቅርቦት፤ በገቢ እቃዎችና ኢኮኖሚው በሚያንቀሳቅሱ ሰራተኞች ላይ በሚጣል ክልከላዎች እንዲሁም የዋጋ ተለዋዋጭነት እንደ ምክንያት ይጠቀሳሉ፡፡ በቁጥር ብዙ የሆኑ ኢትዮጵያዊያን ኑሯቸው የተመሰረተው ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ሁኔታ ውስጥ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉግዜ ገዝተው መመገብ ስለማይችሉ በሽታው ከፍተኛ ጉዳት በሚያደርስበት ግዜ እነዚህ የህብረተሰብ ክፍሎች ለምግብ ዋስትናና የተመጣጠነ ምግብ አቅርቦት ችግር በቀላሉ እጅ እንዲሰጡ ያስገድዳቸዋል፡፡

## 2.7 የስልጠና እና ክትትል መስተጓጎል

በኮቪድ-19 ምክንያት ብዙ ፕሮጀክቶች ከመደበኛ የፕሮጀክት ስራ እና የግብርና ኤክስቴንሽን ግንኙነት ውጪ ሆነዋል፡፡ ስለዚህ የፕሮጀክት እና የኤክስተንሽን ተጠቃሚዎች የተለመደው የአቅም ግንባታ ስልጠና፣ ልምድ ልውውጥ እና ተመሳሳይ ስራዎች እየሰሩ አይደለም፡፡

## 3. የአግሮኢኮሎጂ ግብርና በኮቪድ-19 ላይ ያለው አስተዋፅኦ

የኮቪድ-19 ችግር ዓለም አቀፋዊ ስለሆነ የሰው ልጅ ህይወት እና ኑሮ በእጅጉ ተዛብቷል፡፡ የችግሩ ስፋት እና ጥልቀት ቤቱ ይቁጠረው የሚያስብል ሲሆን በመጠኑም ቢሆን ግን የስነ-ምህዳራዊ ግብርና ግን የኮቪድ-19 ችግርን የመቋቋም ምሳሌ ለመሆን ችሏል፡፡ ለመጥቀስ ያህል፡-

### 3.1 የአገር በቀል የድህረ ምርት ፈጠራዎች መሰረት መሆን

አንዳንድ ምርቶች በተለይ ቲማቲም፣ ድንች፣ ጎመን ወዘተ በገበያ እጦት ምክንያት ለብልሽት እንዳይዳረጉና ገበሬው እንዳይከስር ለማድረግ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ተሞክረው ውጤታማነታቸው የታየው የድህረ ምርት አያያዝ ብቅ እያሉ ነው፡፡ ቢሆንም የድህረ-ምርት ስራዎችን እና የእሴት መጨመር ማቀነባበርያ ዘዴዎችን በተግባር ላይ ማዋል ግዜ ሊሰጠው የማይገባ የቤት ስራ መሆን አለበት፡፡ ለምሳሌ የቲማቲም ድልህና የቲማቲም ቋንጣ ማዘጋጀት፤ ድንች በዱቄት መልክ መስራት፤ የማንጎ ማልማላታ፤ የጎመን ድርቆሽ እና ሌሎችም ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የድህረ-ምርት አያያዝ ቴክኒኮች በማሰልጠን የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ሳይበላሹ ለረጅም ግዜ እንዲቆዩ በማስቻል አምራቹም ይሁን ተጠቃሚው ማህበረሰብ በአሰራር ዘዴዎቹ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ያደርገል፡፡ የፔልም ኢትዮጵያ የተወሰኑ ሙከራዎች እያደረገ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ የማንጎ እና የፕሪም ማልማላታ ሰርቶ ለገበሬዎች እያስተማረ ይገኛል፡፡

### 3.2 የተፈጥሮ ማዳበርያና የተባይ መከላከያ ውሁዶችን ማዘጋጀት እና መጠቀም

በማዳበርያ በኩል ስንመለከት ሰው ሰራሽ የሆነውን ግብአት በሚገባ ተክተው ጥቅም ሊሰጡ የሚችሉ አይነተኛ ተፈጥራዊ ማዳበርያዎችን ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ በአካባቢው ከሚገኙ የተለያዩ አረንጓዴ ቅጠላቅጠሎችን በመሰብሰብ ፈሳሽ ማዳበርያ ማዘጋጀት ይቻላል፤ ከሌሎች ግብአቶች ጋር ማደባለቅም ይቻላል ለምሳሌ ከእበትና ከእንስሳት ሽንት፡፡ በሌላ በኩል የቨርሚ ኮምፖስት ትሎችን ማራባትና መጠቀም፡፡ እነዚህ ፍቱን አማራጮች ተግባር ላይ ከዋሉ ወጪ በከፍተኛ ሁኔታ ይቀንሳል፣ ለሰውና ለአካባቢ ጤናማነት የሚስማማ ይሆናል፣ ሰው ሰራሽ ግብአቶች የምንጠብቅበት ምክንያት አይኖርም፣ አድካሚም አይደለም በቀላሉ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ስለዚህ እነዚህ በአካባቢያችን የሚገኙ ግብአቶች የሚጠቀሙ አግሮኢኮሎጂው የሚስማሙ የተለያዩ አሰራሮችን በማስተዋወቅና ለተግባራዊነታቸው ከፍተኛ ክትትል በማድረግ የአምራች አርሶአደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች ችግሮች ቀጣይነት ባለው መልኩ መፍታት እንደሚቻል ታይቷል፡፡

## 3.3 የጓሮ አትክልት ማምረት

የጓሮ አትክልት በገጠራቱ ኢትዮጵያ የተለመደ ነው፡፡ በቀላል ዘዴ እና ቦታ የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን ያመርታሉ፡፡ ፔለም ኢትዮጵያ በበረሃማ አካባቢዎች የጀመረው ስርጉድ መደብ (Trench Gardening) የአተካከል ዘዴ ነው የተለያዩ አትክልቶችን በአንድ ግዜ ማምረት የሚያስችል ሲሆን በተለይ ራቅ ያለ ቦታ የሚኖሩ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች በደንብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ አስችሏል፡፡ ይህ አሰራር ፔለም ኢትዮጵያ እንደ ብራንድ የሚታወቅበት ሲሆን በዚህም በተለያዩ የፕሮጀክት ቦታዎች ተሞክሮ ከፍተኛ ውጤት ተገኝቶበታል፡፡ ቴክኖሎጂው ውሃ ቆጣቢ ነው፣ በማንኛውም የቤተሰቡ አባል በቀላሉ መሰራት ይችላል፣ ዓመት ሙሉ ምርት አለ፤ ገበያ መሄድ አይጠበቅባቸውም፣ በዚህም በግቢ ውስጥ በማዘጋጀት ከሰው ንክኪ እንድንታቀብ ያስችላል፤ ጤናማ ምግብ እንመገባለን፤ የምግብ ዋስትና እና የተመጣጠነ ምግብ በማስገኘት/በሚሟላት በኩልም ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

ትሬንች ጋርድን አሰራሩን በመቀያየር ለከተማ ግብርና እንደአማራጭ መጠቀም ይችላል፡፡ በአሁኑ ሰዓት የከተማ እና የገጠር ሰው እቤት እየዋለ የአትክልት ምርት ገበያ ባጣበት ወቅት፣ ምርቱ ቢገኝም በተወደደበት ወቅት እቤት ታግተው የሚውሉ ሰዎች ለብዙ ዓላማ ማዋል ይችላሉ፡፡ እነሱም የጓሮ አትክልት ስራን እንደ ጊዜ ማሳለፊያ መጠቀም፣ እቤት ውስጥ ያለው የሰው ጉልበት አምራች እንዲሆን ማድረግ፣እቤት በመዋል የሚፈጠረው የስነልቦና ችግር ለማስወገድና የሰውነት እንቅስቃሴ እንዲኖር ማስቻል፤ የአገሪቱ በኢኮኖሚ መቀዛቀዝ ጫናው እናቶች ላይ ስለሆነ እናቶችን እና ቤተሰብን አትክልት በማምረት ማገዝ፡፡

## 3.4 ጥምር እርሻ (አግሮፎረስትሪ) ማስፋፋት

ዘርፈ ብዙ ጥቅም ያላቸው የዛፍ ፍራፍሬዎችን በመትከል አካባቢያችን ከአየር ለውጥ ችግሮች እየጠበቅን ተጨማሪ የገቢ (ኢኮኖሚያዊ ጥቅም) ምንጭ እንዲኖረን ያስችላል፤ የተመጣጠነ ምግብ እንድናገኝ ያስችለናል፤ የምግብ ዋስትና በማስጠበቅ በኩልም ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

## 3.5 ማህበረሰብ-አቀፍ ንቅናቄዎችን ማከናወን

አብዛኛው አርሶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ቋሚ አትክልቶች ባይለመዱም ለአመት ቀለቡ የሚሆን እህል ይቋጥራል፡፡ በየአካባቢው የተቸገሩ ሰዎች ሲኖሩ ደህና ክምችት ያለው ገበሬ ለሌለው በአይነት እንዲደጋገፍ ለማስቻል ንቅናቄ መፍጠር ይቻላል፡፡ ይህ የመተባበር በጎ አሰረር በወረርሽኙ ወቅት ብቻ ሳይሆን በደህና ግዜም ይዞት የመጣው በጥቂቱ ቢሆን የመደጋገፍ ፍላጎት ወደተሻለ ደረጃ እንዲያሳድ ማስተባበርና ድጋፍ መስጠት ተገቢ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም እህል በከተሞች እጥረት በሚያጋጥምበት ወቅት አምራቹን በተደራጀ መልኩ በማስተባበር ምርቱ እንዲሸጥ የሚቻልበት እድል መፍጠር ይቻላል፡፡

## 3.6 አሳታፊነትን ማበረታታት

ስነ-ምህዳሩን መሰረት ያደረጉ የግብርና አሰራሮች በመሰረቱ የሰዎችን አሳታፊነት ያበረታታሉ። በመሆኑም ተማሪዎች በቤት በሚሆኑበት ወቅት ወላጆቻቸውን በቀላሉ እንዲያግዙና በተለይ የሰው (ሰራተኛ) እጥረትን የሚቀንስላቸው በመሆኑ ምርታቸው በሰአቱ ለገበያ ለማድረስ ያስችላል። እንዲሁም በሌሎቹ የአባዋራው አባላት ማለትም ሴቶች፣ ሽማግሌዎች መሆናቸው የስራ ጫና እንዲቀንስም ያደርጋል።

በተጨማሪም የአግሮኢኮለጂ ዘዴዎች (ከአይነታቸው እና አሰራራቸው ተስማሚነት ባሕሪይ አንፃር) ከበሽታው ጋር ተያይዞ የሚመጣ መጨናነቅ በማስቀረት በኩል ትልቅ ሚና ይጫወታሉ በተለይ ርቀታቸውን ጠብቀው እንዲሰሩ በማስቻል።

## 3.7 በኮቪድ-19 ምክንያት ያጋጠሙ ተግዳሮቶች

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሰርትየም ስነምህዳሩን (አግሮኢኮሎጂውን) መሰረት ያደረገ የግብርና ልማት ስራዎችን ከአባል ድርጅቶች ጋር በመሆን በመስራት ላይ ሲሆን በዚህም የገበሬዎች እና ከፊል አርብቶ አደሮች ምርትና ምርታመነትን በመጨመር የህብረተሰቡን ኑሮ ለማሻሻል እንዲያስችል ተብሎ ፕሮጀክቱ በአምስት ክልሎች በተለያዩ 6 ወረዳዎች ማለትም በአፋር (ኩነባ፣ ስሙሮቢ ገላአሎ)፣ በትግራይ (አፅቢ ወንበርታ)፣ በአማራ (አምባሰል)፣ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ (አሶሳ)፣ በደቡብ (አርባምንጭ) እና በአዲስ አበባ ውስጥ በመሰራት ላይ ይገኛል።

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሰርትየም እና አባል ድርጅቶቹ በሽታው በአገራችን መግባቱን ከተገለፀበት ግዜ ጀምሮ በሚንቀሳቀሱበት የፕሮጀክት ወረዳዎች ላይ የሚገኙ ተጠቃሚ አርሶአደሮች፣ አርብቶአደሮች እና ከፊል አርብቶአደሮች ላይ በሽታው በመግባቱ ብዙ ችግሮች አጋጥሟል። የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል፡-

- የህብረተሰቡ በበሽታው ላይ ያላቸው ግንዛቤ አናሳ በመሆኑ ግራ ተጋብቷል።
- ግንዛቤው ያላቸው ደግሞ የግል ንፅህና መጠበቅያ አቅርቦት አለማግኘት። በገጠር በተለይ ደግሞ በአርብቶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር የውሃ አቅርቦት አለመኖር ችግሩ አባብሶታል። ጫናው በሴቶች እና ህፃናት ላይ ከበድ ይላል።
- ለገበያ ታስበው የተመረቱ አትክልት እና ፍራፍሬ በእንቅስቃሴ ክልከላ ምክንያት ገበያ ስላላገኙ እና ማቆያ ስለሌለቸው የምርት ብክነት ወይም ለብልሽት ተዳርጓል።
- በአብዛኛው የፕሮጀክት ቦታዎች ክትትል፣ ስብሰባ እና ስልጠና ባለመደረጉ መቀዛቀዝ ታይቷል።

## 3.8 ለኮቪድ-19 የተደረገ ፈጣን ግብረ-መልስ

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሰርትየም እና አባል ድርጅቶቹ በሽታው በአገራችን መግባቱን ከተገለፀበት ግዜ ጀምሮ በሚንቀሳቀሱበት የፕሮጀክት ወረዳዎች ላይ የሚገኙ ተጠቃሚ አርሶአደሮች፣ አርብቶአደሮች እና ከፊል አርብቶአደሮች ላይ በሽታው ከቁጥጥር ውጭ ከመሆኑ እና ከፍተኛ

ጉዳት ከማድረሱ በፊት ለመከላከል እንዲያስችል በሚል የተለያዩ ጠቃሚ ስራዎች በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡-

- ከሌሎች ተባባሪ ባለድርሻ አካላት በጋራ በመሆን በበሽታው ምንነትና የመከላከያ ዘዴዎች ላይ ያለውን የማህበረሰቡ ግንዛቤ ለማስፋትና ግብረ መልሶቻቸውን የተሻሉና የተቀናጁ እንዲሆኑ ለማስቻል የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም ተከታታይ የመረጃ ልውውጥ አድርገዋል፤ በሽታውን በተመለከተ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ መልእክቶች ለማህበረሰቡ እንዲሰራጭ አስችሏል፡፡
- ፔለም ኢትዮጵያ ከፕሮጀክት አስፈፃሚ አባል ድርጅቶቹ ጋር በመረዳዳት ፕሮጀክቶቹ በሚገኙባቸው ወረዳዎች ያሉ ተጠቃሚ የማህበረሰብ ክፍሎች ያሉበት ነባራዊ ሁኔታ ምን እንደሚመስል፤ እንዲሁም ድርጅቶቹ ምን ለመስራት/ለማገዝ እንዳቀዱ ወይም ምን እንደሚፈልጉ እቅዶቻቸውን እንዲያቀርቡ በጠየቀበት መሰረት ተግባራዊ አድርጓል፤ በዚሁም አማካይነት በአባል ድርጅቶች አስፈፃሚነት ፕሮጀክቶቹ በሚገኙባቸው ወረዳዎች ወረርሽኙ ለመከላከል የሚያስችሉ ቁሳቁሶች የንፅህና መጠበቂያ ሳሙናዎች፣ አልኮሎች፣ የእጅ ጓንት፣ ሳኒታይዘሮች፣ የአፍና አፍንጫ መሸፈኛ ጭምብሎች፣ የሙቀት መለኪያ መሳርያዎች እንዲሁም ለውሸባ የሚያገለግል ፍራሽ ግዢ ከብሬድ ፎር ዘ ወርልድ በተገኘ ድጋፍ በማከናወን ተበርክተዋል፡፡
- በአሁኑ ሰዓት ያለው የመንቀሳቀስ እግድ ስልጠና ለመስጠት አስቸጋሪነት ለሁሉ ቢሆንም ፔለም ኢትዮጵያ ግን የገበሬ ባለሙያዎች የመፍጠር ዓላማ የጀመረባቸው ቦታዎች በተለይ በኮነባ፣ ሰሚ ሮቢ ገላፅሎ፣ አፅቢ ወንበርታ፣ በአምባሰል፣ እና በአሶሳ ወረዳዎች የቅርብ የስልጠና እና የምክር አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡
- የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች በየቤታቸው በአግሮኢኮለጂ ግብርና የተሰሩ የተለያዩ መልካም ስራዎች የቤተሰብ የምግብ አቅርቦት መስጠታቸው መገንዘብ ይቻላል፡፡ በነሱ ግምገማ በቀጣይነትም የማህበረሰቡን ኑሮ ለማሻሻል የተሻለ ስራ ለመስራት ከዚህ የበለጠ እንደሚሰሩ ይገመታል፡፡

## 4. ማጠቃለያና አስተያየት

በአጠቃላይ የወቅቱ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ያደረሳቸው ጉዳቶች በተመለከተ የተለያዩ ሐሳቦች ተነስተዋል። ለምሳሌ የወረርሽኙ ስፋት በአለም እና በአገራችን ምን ይመስላል፣ በአገራችን ያደረሳቸው ዘርፈ-ብዙ ተግዳሮቶች፣ የፔለም ኢትዮጵያና አባላቶቹ ግብረ-መልስ፣ የአግሮኢኮሎጂ አማራጭ መፍትሔ አሰራሮች በሚል በመጠኑም ቢሆን ለመዳሰስ ተሞክረዋል። የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በአፍሪካም ይሁን በአገራችን ቀስበቀስ እየተስፋፋ ይገኛል። እስከአሁን የታዩት እና የሚያስከትላቸው አገራዊ ተግዳሮቶች በትንሹ ቢሆንም ለማየት እንደተቻለው ከሆነ ገና ሳይስፋፋ እነዚህ ችግሮች ካጋጠሙ ይበልጥ ስፋቱ በሚጨምርበት ወቅት ምን ሊያስከትል እንደሚችል ለመገመቱ አዳጋችና አስፈሪ ያደርገዋል።

ስለሆነም ከችግሩ ለመላቀቅ በግል የምንሰራቸው ስራዎች ለብቻቸው አመርቂ ውጤት አያመጡም፤ አደጋውን ለመሻገር ሁሉም ባለድርሻ አካላት ለእያንዳንዱ ችግር በመነጋገር የመፍትሔ ሀሳብ በማመንጨት በተባበረ ክንድ እና በተቀናጀ መልኩ መስራት ይጠበቅባቸዋል። በተለይ በአገራችን አብዛኛው ማህበረሰብ ኑሮው በግብርና የተመሰረተ እንደመሆኑ መጠን ስነምህዳሩ የጠበቁ አሰራሮች እንዲተገበሩ መረባረብ መቻል ምግብ ዋስትናን ከማስጠበቅም አልፎ የአገሪቱ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት ሁኖ እንዲቀጥል ያስችላልና በትኩረት መሰራት አለበት።

ሆኖም የአገሪቱ ኢኮኖሚ መቀዛቀዝ እና የአምራቹ ህብረተሰብ ተስፋ መቁረጥ እንዳይኖር የተለያዩ የመፍትሄ አማራጮች መጠቀም ለምሳሌ የማሳ እና የድህረ ምርት ጥንቃቄዎች መጠቀምን፣ የገበያ ትስስርን፣ የምርት እሴት መጨመርን፣ የአካባቢ (የአርሶ-አደር፣ አርብቶ-አደር እና ከፊል አርብቶ አደር) ባለሙያ በመፍጠር ቀጣይነት ያለው ልምድ፣ ምክር እና ስልጠና አገልግሎት መስጠትን፣ ወዘተ።

ፔለም ኢትዮጵያ ኮንሰርትየምም ከአባል ድርጅቶቹ፣ ከተባበሪ እንዲሁም ከሚመለከታቸው ባለ ድርሻ አካላት ጋር በመተባበር የአገሪቱን ተግዳሮቶች በተለይ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚው እና ተያያዥ ማነቆዎች ለመፍታት አግሮኢኮለጂውን ማእከል ያደረጉ አሰራሮችን በመተግበር፣ እንዲተገበሩ በማስተባበርና በማገዝ በኩል ከፍተኛ ስራ እየሰራ ሲሆን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግም በርትቶ እንደሚንቀሳቀስ ለመግለፅ ይወዳል።